# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላምና በጤና አደረሳችሁ



# በድሬደዋ ሀገረ ስብከት የሰ/ት/ቤቶች ማዳራጃ

# የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ተዝጋጅቶ የቀረበ

# ለመስቀል ደመራ በዓል በድሬደዋ ባሉ ሰ/ት/ቤቶች የሚዘመሩ የመስቀልና የምስጋና መዝሙራት

መስከረም 2013 ዓ

**የመስቀል አጫጭር መዝሙራት**

1. በመስቀልከ
2. መስቀልከ
3. በመስቀሉ
4. መስቀል ኃይልነ
5. መስቀል ብርሃን
6. መስቀል ብርሃን /ወሀቤ/
7. እሌኒ ንግሥት
8. መስቀል አብርሃ
9. ኃይልነ
10. ዮምሰ ለእሊአየ
11. ለክብረ ዝንቱ
12. ወሪዶ እመስቀሉ
13. ጥልን በመስቀሉ
14. ከመ ትባርከነ
15. በእንተ ዝንቱ
16. በወንጌሉ
17. ይቤሎሙ
18. ፀጋ ነሳዕነ
19. ዝንቱ መስቀል
20. የጌታችን መስቀል
21. እንተ ተሐንፀት
22. ዘዕጣን አንፀረ
23. ኅበሩ ቃለ
24. ዮም በዓለ መስቀሉ
25. ኧኸ በመስቀልከ
26. መስቀል አብርሃ /አዲሱ/

**የመስቀል ረጃጅም መዝሙራት**

1. መስቀል ተመርኩዘን
2. መስቀል ሕይወት
3. ደስ ይበለን
4. ኀበ ቀራንዮ
5. መስቀል አበባ
6. መስከረም ጠባ

**የምስጋና አጫጭር መዝሙራት**

1. ንጉሥ ውእቱ ዘለዓለም
2. ንጉሥ ውእቱ
3. ሠራዊተ
4. ዘምሩ
5. እንተ በምድር
6. መልአከ ሰላምነ
7. ጼና አልባሲሁ
8. ለተክለሃይማኖት ጻድቅ
9. ኢትዮጵያ ታበጽሕ
10. እንዘ ይብሉ
11. ጽላት ዘሙሴ
12. ልዑል ውእቱ
13. እሳት ጽርሁ
14. መሠረተ ዜማ
15. ለሃገሪትነ
16. ክነፈ ርግብ
17. ለእመ መሐርከነ
18. መንክር ግርማ
19. አርሴማ ቅድስት
20. እርሱ እንደ ንብ
21. መድኃኔዓለም አዳነን
22. ክንፉ ጸለላ
23. መሠረተ ሕይወት
24. ዓይኑ ዘርግብ
25. በበግማድ
26. ሶበ መተርዎ
27. ኀበ አምደ ወርቅ
28. ሰባኬ መድኃኒት
29. ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት
30. አቡነ ኪሮስ
31. ያሬድ ወጠንከ
32. እመቤታችን
33. ማርያም ተዓቢ
34. የኪዳን ጸላት
35. ይዌድስዋ
36. በመኑ
37. ውእቱ ሊቆሙ

38. ተናገሩ
39. የወንጌል ቡቃያ
40. ጊዮርጊስ ኃያል
41. ገብረ መንፈስ ቅዱስ
42. ሚካኤል ሊቅ
43. ምስለ ሚካኤል

**ረጃጅም የምስጋና መዝሙራት**

1. የሥላሴን  መንበር
2. ኑ በእግዚአብሔር
3. እልል በሉ
4. ይለመነናል
5. ንሴብሖ ለእግዚአብሔር
6. አንደበቴም ያውጣ
7. ከክርስቶስ ፍቅር
8. የመስቀሉ ፍቅር
9. ደስ ይበለን በጣም
10. በምን በምን
11. እመቤቴ የአምላክ እናት
12. ለማርያም
13. ትህትናሽ
14. በጎ መዓዛ
15. ነዓ ነዓ
16. የስሙ ትርጓሜ
17. እልፍ አዕላፋት
18. ጻድቃን ሰማዕታት
19. ኦ ፍጡነ ረድኤት
20. ገድሉ ተዓምራቱ
21. ያሬድ ካህኑ
22. የቅዱሳን በዓት
23. ታማልደናለች
24. ንሴብሖ ለሥላሴ
25. አምላከ እስራኤል
26. አማልደን ስንልህ
27. ሰዓሉ ለነ
28. ለዓለም ሰበኩ
29. አንቺን የያዘ ሰው
30. ናና ሚካኤል ናና
31. ማርያም እንወድሻለን
32. ምሥራቅ ናት
33. ሞት ነው ረሃብ
34. ወዳጄ ሆይ
35. ተክለሃይማኖት ተክለአብ
36. የሕይወትን መዝገብ
37. በዘባነ ኪሩብ
38. ደስ ይበልሽ
39. ጋሻውን ይዞ
40. ቤተ ክርስቲያን
41. ፅኑ ሰማዕት
42. ትንሳኤሽን ያሳየን
43. ተዋሕዶ
44. ኦ ክርስቶስ
45. ከወገኔ ጋራ
46. ደስ ይበለን
47. ነይ ነይ
48. ስምሽን ጠርቼ
49. ሥላሴን አመስግኑ
50. የቤሩቱ ኮከብ
51. የብርሃን አክሊል ናት
52. ወደ ማደሪያው
53. ውዳሴ ማርያም
54. ቅዱስ ሚካኤል
55. ለምኚ ድንግል ለምኚ
56. ይበራል በክንፉ
57. ኃያል ነህ አንተ
58. የፍቅር እናት

**የመስቀል አጫጭር መዝሙራት**

1. **<u>በመስቀልከ</u>**

በመስቀልከ ርድአነ
ወበኃይልከ ተማኅፀነ(2)

2. **<u>መስቀልከ</u>**

መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ (2)
ይኩነነ ቤዛ /4/ መስቀልከ ይኩነነ ቤዛ
**<u>ትርጉም፡-</u>** መስቀልህ ቤዛ ይሁነን (2)
ቤዛ ይሁነን /4/ መስቀልህ ቤዛ ይሁነን

3. **<u>በመስቀሉ</u>**

በመስቀሉ ወበቃሉ
አዕበዮሙ ለአበዊነ /2/

4. **<u>መስቀል ኃይልነ</u>**

መስቀል ኃይልነ መስቀል ፅንዕነ መስቀል ቤዛነ
መድኃኒትነ ለእለ አመነ (2)

5. **<u>መስቀል ብርሃን</u>**

መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም
መሠረተ /3/ ቤተክርስቲያን
**<u>ትርጉም፡-</u>** መስቀል ብርሃን ነው ለዓለሙ ሁሉ
መሠረትነው /3/ የቤተክርስቲያን

6. **<u>መስቀል ብርሃን</u>**

መስቀሉ ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተክርስቲያን
ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም መስቀል መድኅን ለእለ
ነአምን
**<u>ትርጉም፡-</u>** መስቀል ብርሃን ነው ለመላው ዓለም
መሠረት ነው የቤተክርስቲያን
ሰላምን ሰጪ ነው መድኃኔዓለም መስቀል አዳኝ ነው
ለምናምን ሰዎች

7. **<u>እሌኒ ንግሥት</u>**

እሌኒ ንግሥት ኀሠሠት መስቀሎ
ዕንባቆም ነቢይ ዘአንከረ ግብሮ /2/

**<u>8. መስቀል አብርሃ</u>**

መስቀል አብርሃ /2/ በከዋክብት
አሰርገወ ሰማየ በከዋክብት (2)

**<u>9. ኃይልነ</u>**

ኃይልነ ወፀወንነ ወሞገስነ (2)
ዝንቱ ውእቱ መስቀል /2/
**<u>ትርጉም፡-</u>** ይህ መስቀል ኃይላችን
ሞገሳችን መጠጊያችን ነው

**<u>10. ዮምሰ ለእሊአየ</u>**

ዮምሰ ለእሊአየ
አበርህ በመስቀልየ (2)
**<u>ትርጉም፡-</u>** ዛሬ ግን ለወገኖቼ
አበራለው በመስቀሌ (2)

**<u>11. ለክብረ ዝንቱ</u>**

ለክብረ ዝንቱ መስቀል ክርስቶሳውያን
ንሰግድ /5/ ለዕፀ መስቀሉ

**<u>12. ወሪዶ እመስቀሉ</u>**

ወሪዶ እመስቀሉ
እመስቀሉ አብርሃ ለኵሉ /2/

**<u>13. ጥልን በመስቀሉ</u>**

ጥልን በመስቀሉ ገደለ
በመስቀሉ ለሰው ልጅ ሰላምን አደለ (2)

**<u>14. ከመ ትባርከነ</u>**

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ <u>ዘወርቅ</u> /2/
ተዋነይ በጽድቅ /4/ ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ

**<u>15. በእንተ ዝንቱ</u>**

በእንተ ዝንቱ አዘዙ መምህራነ ቅዱስ ወንጌል (2)
ንስግድ ለመስቀል /2/ ወለማርያም ድንግል

**<u>16. በወንጌሉ</u>**

በወንጌሉ ያመናችሁ /2/
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ /2/

**<u>17. ይቤሎሙ</u>**

ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአይሁድ እመኑ ብየ
ወእመኑ በአቡየ አበርህ /2/ በመስቀልየ

**<u>18. ፀጋ ነሳዕነ</u>**

ፀጋ ነሳዕነ ወሕይወተ ረከብነ

በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ በኃይለ መስቀሉ
ኪያከ እግዚኦ ነአኲት
ወንሴብሐከ እግዚአብሔር

**19. ዝንቱ መስቀል**

ዝንቱ መስቀል ቤዛነ መድኃኒትነ
ዝንቱ መስቀል ቤዛነ መድኃኒትነ /2/

**20. የጌታችን መስቀል**

የጌታችን መስቀል መመኪያችን
ለዓለም የሆነው አርአያ
መድኃኒት ሊሆነን መጣልን ለኢትዮጵያ

**21. እንተ ተሐንፀት በስሙ**

እንተ ተሐንፀት በስሙ ወተቀደሰት በደሙ
ቤተክርስቲያን
ወተአትበት /2/ በዕፀ መስቀሉ
እስመ ኃይለ እግዚአብሔር ላዕሌሃ

**22. ዘዕጣን አንፀረ**

ዘዕጣን አንፀረ (2*)
በጎልጎታ ተረክበ ዕፀ መስቀል (2*)

**23. ኅበሩ ቃለ**

ኅበሩ ቃለ ነቢያት
ወይቤሉ መስቀል ብርሃን /2/ ለኲሉ ዓለም

**24.ዮምበዓለመስቀሉ**

ዮም በዓለ መስቀሉ በሰማያት በላዕሉ (2*)
ወዘነግሠ በምድር (2* ) ለአሕዛብ (2*)

**25.ኧኸ በመስቀልከ**

ኧኸ በመስቀልከ ኧኸ ጽልመተ አብራህከ
ኧኸ በመስቀልከ ኧኸ ሙታነ አንሣእከ
ኧኸ ወዘተኀጕለ ረዳእከ በመስቀልከ

**26 . መስቀልአብርሃ**

መስቀል አብርሃ በክዋክብት አሠርገወ ኢትዮጵያ (2*)
እምኲሉሰ ፀሐየ አርአየ እግዚአብሔር (2*)

## የመስቀል ረጃጅም መዝሙራት

**1. መስቀል ተመርኲዘን**

መስቀል ተመርኲዘን ወንጌል ተጫምተን
ሃይማኖትን ሰብከን በክርስቶስ አምነን
ማን ያሸንፈናል እኛ ክርስቲያንን
ክርስቶስ አለልን
ንግስቲቷ እሌኒ በጣም የታደለች
በዕጣን ጢስ ተመርታ መስቀሉን አገኘች
መድኃኒት ስትፈልግ ኪራኮስን ይዛ
መስቀሉን አገኘች የዓለሙን ቤዛ

ሙታንም ተነስተው ያመሰገኑት
ዕፀ መስቀሉ ነው የእኛ መድኃኒት
መስቀል ምርኲዛችን ጎዳናው ወንጌል
ወደ ገነት እንጂ አንሂድም ሲኦል
ንዑ ንወድሶ በዕለተ መስቀል
የተሸከመውን የአምላክን ቃል
ንዑ ንወድሳ ለማርያም ድንግል
አክሊለ ምዕመናን ምክሓ ደናግል

**2 . መስቀል ሕይወት**

መስቀል /2/ ሕይወት መግቢያ ለገነት
በመስቀል እንመካለን እንድንበታለን
አዝ...
እኛ ስንባረክ ›› ›› በዕፀ መስቀሉ ›› ››
ሰራዊተ አጋንንት ›› ›› ከእኛ ይርቃሉ ›› ››
አይሁዶች በክፋት ›› ›› ከደበቁት ቦታ ›› ››
እሌኒ አገኘችው ›› ›› በዕጣን ጢስ ተመርታ ››
አዝ...
ጌታ በመስቀሉ ›› ›› ተዓምራትን ሰራ ›› ››
ሙታንን አስነሳ ›› ››ዕውራን አበራ ›› ››
የጌታችን መስቀል ›› ›› ለዓለም አርአያ ››
ሊባርከን መጣ ›› ›› ወደ ኢትዮጵያ ›› ››
አዝ...
ብዙ ቦታ እያለ ›› ›› የቅዱሳን ስፍራ ›› ››
እንደምን ተመረጥሽ ›› ›› የአንባሰል ተራራ ››
ግሸን ደብረ ከርቤ ›› ›› ምድረ ጎልጎታ ›› ››
የቀኝ እጁ መስቀል ›› ›› ያረፈብሽ ቦታ ›› ››
አዝ...
እንድትመሰገን ›› ›› በሕይወት በይባቤ ›› ››
እንደምን ተመረጥሽ ›› ›› አንቺ ደብረ ከርቤ››
ግሸን ያንቺን ምድር ›› ›› የረገጠ ሁሉ ›› ››
ቃልኪዳንን ሰጠ ›› ›› በማይሻር ቃሉ ›› ››
አዝ...
አንድ ቀን የቆመ ›› ›› ከበራፍሽ መጥቶ ›› ››
የሰራውን ኃጢአት ›› ›› አላስብም ከቶ ›› ››
እንደ 40 ቀን ሕፃን ›› ›› ሆኖ ይቆጠራል›› ››
ብሎ ቃል ገባላት ›› ›› ለማርያም ድንግል›› ››

**3 . ደስ ይበለን**

ደስ ይበለን እልል በሉ (2)
አልቀረም ተቀብሮ ተገኘ መስቀሉ (2)
በብርሃን መላት ዓለምን በሙሉ (2)
ምን ቢተባበሩ ምቀኞች ቢጥሩ(2)
ቅዱስ መስቀሉንም ሸሽገው ቢሰውሩት (2)
አልቻሉም ሊያጠፉት ምን ቢተባበሩ (2)
በተራራ ተሰውሮ ለዘመናት (2)
ተጥሎ በተንኮል ተሰውሮ ከኖረበት (2)
ተገለጠ እነሆ በደመራ እሳት (2)
እሌኒ ናት ይህን መስቀል ያስገኘችው (2)
ደመራን በጥበብ በቦታው ያስቆመችው (2)
የተንኮልን ተራራ ያስቆፈረችው (2)
ታሪካዊ የክርስቶስ ህያው መስቀል (2)
ይኸው ተገለጠ በክብር በግሩም ኃይል (2)
ምን ጊዜም ሲያበራ እንዲህ ይኖራል (2)

**4 . ኀበ ቀራንዮ**

ኀበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት
ቀራንዮ /2/ ሐበቀራንዮ
የመስቀሉ ቃል ለኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው
ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለኛ ግን ሕይወት ነው
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ
እንመነው አንካደው አማኑኤል ቸር ነው
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት
እንመናት አንካዳት የአምላክ እናት ናት

**5 . መስቀል አበባ**

መስቀል አበባ ነህ ውብ አበባ
አደይ አበባ ነሽ ውብ አበባ
አዝ...
›› ›› ጥራጊውን ሞልተው ›› ›› አይሁድ በክፋት
›› ›› ጢሱ ሰገደ ›› ›› መስቀል ካለበት
›› ›› ተቀብሮ ሲኖር ›› ›› ስነ ስቅለቱ
›› ›› እሌኒ አገኘች ›› ›› ደገኛይቱ
አዝ...
›› ›› ግማደ መስቀሉ ›› ›› የጌታችን
›› ›› ምስለ ፍቁር ወልዳ ›› ›› እመቤታችን
›› ›› የሚካኤል ፅላት ›› ›› ይዘው ታቦቱን
›› ›› መስከረም በባተ ›› ›› በ10ኛው ቀን
›› ›› ከግብፅ ወጣ ›› ›› በዳዊት ዘመን
አዝ...
›› ›› መስቀሉንም ወስደው ›› ›› ከመስቀሉ ስፍራ
›› ›› በግሸን አኖሩት ›› ›› በአንባሰል ተራራ
›› ›› የመስቀሉ ዜና ›› ›› ደስታን አበሰሩ
›› ›› አሽብርቀው ደምቀው ›› ›› ለእርሱ መሰከሩ
አዝ...
›› ›› የመስቀሉ ስም ›› ›› ተዓምራትን ሰራ
›› ›› ድውይን ፈወሰ ›› ›› እውራን አበራ
›› ›› ለምፃሙም ነፃ ›› ›› ጎባጣውም ቀና
›› ›› አጋንንትም ወጡ ›› ›› ከሰው ልጅ ልቡና
›› ›› ፍቅር አንድነት ›› ›› ሆኖልናልና

**6. መስከረም ጠባ**

መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ /2/ ኢ
መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ ኢዮ
መስከረም ጠባ ለእኛ ኢዮሃ አበባ
መስቀል ጠባ ኢዮሃ አበባ
ለእኛ እንዲሆነን እድገትና ልማት
ኢዮ ኢዮ አበባዬ ኢዮ
መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ
በተዋሕዶ የከበረች እናታችንን
የጥበብ ልጆቿ እናከብራታለን
ሃይማኖት ከምግባር ወንጌልን መግባ ስላሳደገችን
የድኅነት መሰረት ቤተክርስቲያን እናታችን

ጥንትም መሪና አስተማሪ በመሆኗ
በዓለም ላይ ታውቋል ዜናዋ
እየተወሳ በዓለም ዜና ያኮራናል መስቀላችን
ኢዮሃ አበባ መስከረም ጠባ
ኢዮሃ አበባ /3/

**የምስጋና አጫጭር መዝሙራት**

1. **ንጉሥ ውእቱ**

ንጉሥ ውእቱ ንጉሥ ሰላም
አምላክነ (፪) መድኃኔዓለም

2. **ንጉሥ ውእቱ ዘለዓለም**

ንጉሥ ውእቱ ዘለዓለም ክርስቶስ
ንጉሥ ውእቱ ዘኢይሰዓር መንግሥቱ (2)

3. **ሠራዊተ መላእክቲሁ**

ሠራዊተ መላእክቲሁ
ለመድኃኔ ዓለም(፪) ይቀውሙ (፪)
**ትርጉም** የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮቹ
ይቆማሉ ከፊቱ(፪) አገልጋዮቹ(፪)

### 4. ዘምሩ

ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ (፪)
ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ (፪)

### 5. እንተ በምድር

እንተ በምድር ስረዊሃ ወበሰማይ አዕጹቂሃ
ሐረገ ወይን (፪) ድንግል ሐረገ ወይን
**ትርጉም** ስሮቿ ያሉረት በምድር ቅርጫፎቿ በሰማይ
የወይን ሐረግ (፪) ድንግል የወይን ሐረግ

### 6. መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ዑራኤል
ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ
አዕርግ ጸሎተነ
ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም

### 7. ጼና አልባሲሁ

ጼና አልባሲሁ /2/ ለገብረ መንፈስ ቅዱስ ከመ ጼና ስሂን
አልባሲሁ ዘሜላት (2) ዘወረደ ውስተ ገነት

### 8. ለተክለ ሃይማኖት ጻድቅ

ለተክለሃይማኖት ጻድቅ መጠነ በዝኃ ሕማሙ ትዌድሶ
ደብረ ሊባኖስ ገዳሙ /2/
እስመ በውስቴታ ተገብረ ፍልሰተ ስጋሁ ወአጽሙ እምነ
አድባራት ኵሎን ዘተለዓለት በስሙ
ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ

### 9. ኢትዮጵያ ታበጽሕ

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ (2) ኀበ እግዚአብሔር
እንዘ ትብል አምላኪየ (2) ነጽረኒ ወአድኅነኒ
እምኃይለ ፀላኢ ወፀር

### 10. እንዘ ይብሉ

እንዘ ይብሉ ወይዜምሩ በልሳን ዘኢያረምም አማን
በአማን /2/ መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም(2)

### 11. ፅላት ዘሙሴ

ፅላት ዘሙሴ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና
ፀናፅል /5/ ለአሮን ካህን

### 12. ልዑል ውእቱ

ልዑል ውዕቱ ልዑለ መንበር (2)
ሚካኤል (2) ሊቀ መላእክት (2)

### 13. እሳት ጽርሁ

እሳት ጽርሁ ማይ ጠፈሩ (2)
ደመና መንኰራኵሩ ለመድኃኔ ዓለም (2)

### 14. መሠረተ ዜማ

መሠረተ ዜማ ወጠነ /2/ ያሬድ ካህን
ያሬድ /4/ ካህን /2/

### 15. ለሃገሪትነ

ለሃገሪትነ ሰላማ ኪያከ ተዐቅብ
አባ ኦ (2) ገብረ መንፈስ ቅዱስ (2) አባ

### 16. ክነፈ ርግብ

ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ወገበዋቲሃኒ
ሐመልማለ ወርቅ
አንቲ ምስራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ
አማን በአማን (2) ኢየኃልቅ ኪዳንኪ ወላዲተ አምላክ
**ትርጉም** እንደ ርግብ ክንፍ በብርም እንደተሰራ
ጎኖችሽም ሐመልማለ ወርቅ (2)
አንቺ ምስራቅ ልጅሽም የጽድቅ ፀሐይ ነው እውነት
በእውነት (2) አያልቅም ቃል ኪዳንሽ የአምላክ እናት

### 17. ለእመ መሐርከነ

ለእመ መሐርከነ ትሰመይ መሐሬ መድኃኔ ዓለም
ወለፃድቃንሰ እምግባሮሙ ትሜህሮሙ ለፃድቃን

### 18. መንክር ግርማ

መንከር ግርማ ኃይለ ልዑል ጸለላ
አማን አማን መላእክት ይዌድስዋ (2)
**ትርጉም** በሚያስደንቅ ግርማ የልዑል ኃይል ጋረዳት
በእውነት በእውነት መላእክት አመሰገኗት (2)

## 19. አርሴማ ቅድስት

አርሴማ ቅድስት (3)
ሰማዕት (2) አርሴማ ቅድስት

## 20. እርሱ እንደ ንብ

እርሱ እንደ ንብ አውራ ፈረሱ እንደ አሞራ
ጊዮርጊስ (2) ኢትዮጵያን አደራ (2)

## 21. መድኃኔዓለም አዳነን

መድኃኔዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ
ደስ ይበለን (2) እልል በሉ (2) አዳነን በማይሻር ቃሉ
እናታችን ቅድስት የአምላክ እናት
እንስገድላት (2) እንስገድ (2) በእውነት ለአምላክ እናት
ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ
ያማልዱናል (2) መላዕክት (2) በእውነት በላየኛው ቤት
ተዋሕዶ ሃይማኖት እንከን የሌላት
እንከተላት (2) እስከሞት (2) በእውነት ያለ ፍርኃት

## 22. ክንፉ ጸለላ

ክንፉ ጸለላ (3)
ተፈስሒ ለድንግል ይቤላ (2)

## 23. መሠረተ ሕይወት

መሠረተ ሕይወት ማርያም በረድኤት ነይ
ምህረት ቸርነትን ይዘሽ ከሰማይ (2)
ማርያም ድንግል በረድኤት ነይ

## 24. ዓይኑ ዘርግብ

ዓይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ
ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ (2)

## 25. በበ ግማድ

በበ ግማድ ሥጋሁ መተሩ፣
ቅዱስ (፫) ጊዮርጊስ ሞኦሙ ለፀሩ።

## 26. ሶበ መተርዎ

ሶበ መተርዎ ለጊዮርጊስ ፀሐይ/2/ጸልመ
አድለቅለቀት ምድር ወተከሥቱ ዬ ዬ ዬ።

## 27. ኀበ ዐምደ ወርቅ

ኀበ አምደ ወርቅ (፫)
ተጽሕፈ ስሙ እስጢፋኖስ ኀበ አምደ ወርቅ።

## 28. ሰባኬ መድኀኒት

ሰባኬ መድኀኒት ጎርጎርዮስ አቡነ
ጸሎትከ ትኩነነ ፀወነ።

## 29. ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት

ያሬድ ፈልፈለ ማኅሌት ወቅኔያት ወባሕረ ጥበባት፣
እስመ ኮንከ መርሐ ለዘምሮ ለኢትዮጵያ፣ ያሬድ ካህን
(፪*) ጥዑመ ልሳን።

## 30. አቡነ ኪሮስ

አቡነ ኪሮስ የአምላክ ባለሟል ቅዱስ ናቸው፣
ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ሥራቸው ያበራል ይኸው።

## 31. ያሬድ ወጠንከ

ያሬድ ወጠንከ ነቢበ አንቀጸ ብርሃን፣
አንቀጸ ብርሃን (፫*) ወጠንከ አንቀጸ ብርሃን

## 32. እመቤታችን ማርያም

እመቤታችን ማርያም ሃገራችንን ጠብቂልን በምልጃሽ
ከመናፍቃን ከከሃድያን ከጠላት ሰይጣን ሰውረሽ
እንድትጠብቂን በምልጃሽ

## 33. ማርያም ተዓቢ

ማርያም ተዓቢ እምኵሉ ፍጥረት
ኢያውዓያ እሳተ መለኮት (2)
ማርያም ትበልጣለች ከሁሉ ፍጥረት
ስላላቃጠላት የመለኮት እሳት (2)

## 34. የኪዳን ጸሎት

የኪዳን ጽላት የተሰወረ መና ያለብሽ
ደብተራ ድንኳን አንቺ ነሽ (2)
ይኸውም መና የተባለው/2/
በድንግል ማርያም ያደረው
የእግዚአብሔር አብ ልጁ ነው

### 35. <u>ይዌድስዋ</u>

ይዌድስዋ መላእክት (2) ለማርያም
በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ
በኀኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ

### 36. <u>በመኑ</u>

በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ
እመቤቴ የእኛ አማላጅ አዛኝቱ
ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ

### 37. <u>ውእቱ ሊቆሙ</u>

ውእቱ ሊቆሙ ለመላእክት
ወመልአኮሙ ስሙ ሚካኤል
ልብሱ ዘመብረቅ ዓይኑ ዘርግብ ሊቀ መላእከት

### 38. <u>ተናገሩ</u>

ተናገሩ ድንቅ ሥራውንም መስክሩ
ተዓምሩን ለዓለም ንገሩ (2) ድንቅ ሥራውን መስክሩ

### 39. <u>የወንጌል ቡቃያ</u>

የወንጌል ቡቃያ <u>እምነት አዝመራ/</u>3/
ለምኝልን አማልጅን አስታርቂን እናታችን ክርስቶስ ሠምራ

### 40. <u>ጊዮርጊስ ኃያል</u>

ጊዮርጊስ <u>ኃያል</u> (2) መስተጋድል
ገባሬ ተዓምር/2/ ኮከበ ክብር(2)

### 41. <u>ገብረ መንፈስ ቅዱስ</u>

ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን ናቸው
ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ስራቸው (2)

### 42. <u>ሚካኤል ሊቅ</u>

ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ
ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ (4) ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ

### 43. <u>ምስለ ሚካኤል</u>

ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል እመ አምላክ ንዒ ማርያም
ንዒ (6) እመአምላከ ንዒ ማርያም
ከሚካኤል ከገብርኤል ጋራ የአምላክ እናት ነይ ማርያም
ነይ (6) የአምላክ እናት ነይ ማርያም

## <u>ረጃጅም የምስጋና መዝሙራት</u>

### 1. <u>የሥላሴን መንበር</u>

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሃል ሚካኤልን ከፊት
አዕላፍ መላእክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን አባት
    የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
    እያሸበሸቡ የሰማይ መላእክት
    ካህናተ ሰማይ ቅዱስ (3) ሲሉ
    ይህን ታላቅ ክብር ሊያዩ የታደሉ
    በጽድቅ ስራቸው በምድር ይታያሉ (2)
የቅዱሳን ኅብረት የቅዱሳን ሃገር
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን መንበር
ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ
እግዚአብሔር ያድለን በትንሳኤ እንድናይ (3)

### 2. <u>ኑ በእግዚአብሔር</u>

ኑ በእግዚአብሔር ደስይበለን (2)
ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን
ከሞት ወደ ሕይወት ላሸጋገረን
ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን
    የሰማዩን መንግስት ርስቱንለሰጠን
    ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን
    ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል
    በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል
ከአለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል
ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል
ፍቅርህ የበዛነው ምን ልክፈልህ ጌታ

ስምህን ላወድሰው ከጠዋት እስከ ማታ
በቃዴስ በርሃ ምንም በሌለበት
በኤርትራ ባሕር ወጀብ በበዛበት
ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምንተስኖት
ልባችሁ አይፍራ በፍፁም እመኑት
በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም
ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም
ያጣነውን ሠላም ዛሬ አገኘን
እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን
የሐና የኢያቄም የእምነታቸው ፍሬ
በእግዚብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ
የኢያቄም ስዕለቱ የሐና እምነት
ለምኝልን ለእኛ ኪዳነ ምህረት

### 3. <u>እልል በሉ</u>

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩ ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ
በኃጢአት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትዕዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላለ ጠላቶቹ ሳለን
ውለታው ብዙ ነው ክብር ለእርሱ ይሁን (2)
ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ሥጋውንና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምሥጋና ይድረሰው ለመድኃኔዓለም (2)
ሕይወቱን የሰዋ እንደአምላክ ማን አለ
ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩም አይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ (2)
ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ
ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በእልልታ (2)

### 4. <u>ይለመነናል</u>

ይለመነናል አምላከ አብርሃም
ይታደገናል መድኃኔዓለም
ለፍጥረት ሁሉ እጁን የዘረጋ
ቸር እረኛ ነው አልፋና ኦሜጋ (2)
አብርሃም ይስሀቅን ያዕቆብን አስበህ
የማልክላቸውን ቃልኪዳን አስታውሰህ
ደካማ ለሆንን ሥጋ ሰልጥኖብን
አትመልስ ጌታ የምህረት ዓይንህን
ከሰማየ ሰማይ ይድረስ ጩኸታችን /2/
እንዘን እናልቅስ ስለ በደላችን /2/
ባይመለከተን አምላከ አብርሃም
በምሕረት ዓይኖቹ መድኃኔዓለም
ባይዘረጋልን አምላከ አብርሃም
የፍቅር እጆቹ መድኃኔዓለም
ሕዝበ እስራኤል ሁሉ ለአምላክ ዘምሩ /2/
አድኖናልና በሚያስደንቅ ፍቅሩ (2)
ምንም እንኳን ክህደት ቅስፈት ቢበረታ
ስለ አብርሃም ብለህ አልተውከንም ጌታ
ለቅዱሳን ያለህ ቃልኪዳን ሲጸና
ቀስተ ደመናህን አይተነዋልና
የእስራኤል አምላክ የማታንቀላፋ /2/
በፍቅርህ ታደገን በሞት ሳንጠፋ /2/
ቃልኪዳንህ ግሩም አምላከ አብርሃም
ምህረቱ የበዛ መድኃኔዓለም
ርስት ጉልታችን አምላከ አብርሃም
የህይወታችን ቤዛ መድኃኔዓለም
ሳይጸየፍ ጌታ ያደፈ ኃጢአቴን /2/
ከማጥ ውስጥ አወጣት ታደጋት ሕይወቴን (2)

### 5. <u>ንሴብሖ ለእግዚአብሔር</u>

ንሴብሖ  (2) ለእግዚአብሔር
ስቡሐ ዘተሰብሐ (2)
እናመስግነው (2) እግዚአብሔርን
ምሥጉን ነው የተመሰገነ (2)
ባሕሩን ተሻግረን ወንዙ ደረቅ ሆነ
በጠላታችን ላይ ድሉ የእኛ ሆነ
ከባርነት ቀንበር ፍፁም ነፃ ወጣን
ሕይወት የሚሰጠን መና ነው ምግባችን
ከአለት ላይ ውሃ ፈልቆ የጠጣነው
ይህን ታላቅ ጌታ ኑ እናመስግነው
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል
አስፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉን አለፍነው አምላካችን ይክበር
ጉልበታችን ቢዝል መከራው ቢበዛ
ኃይላችን ጌታ የዓለሙ ቤዛ

### 6. <u>አንደበቴ ያውጣ</u>

አንደበቴ ያውጣ የምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለው በዓይኔ
በገባዖን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ኀብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላፃ ከሞት አተረፈኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኛ ጋር
በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋራ ስዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ
አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣዖት እንድሰግድ ነገስታት ቢያውጁም
ሁሉም ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም
ፅናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኔዓለም

## 7. ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው
መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው (2)
አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም
እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም (2)
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሠራው
ግንቡ ንፁህ ውሃ መሠረቱ ደም ነው (2)
ሳይነጋ ተራምደን እንግባ በጠዋት
በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት (2)
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት
የውሃ ግድግዳ የደም መሠረት (2)
የውሃ ግድግዳ የደም መሠረት
ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት (2)

## 8. የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር ቢገባን /4/
እመቤታችንን እናያታለን
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊተ ዓለም
እናቱ ነሽና ለመድኃኔዓለም
ነይ ነይ እምዬ ማርያም
ነይ ነይ ቤዛዊተ ዓለም
አባ ሕርያቆስ አባታችን
የመስቀሉ ፍቅር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋራ ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር
የምናኔው ጸሎት ልዩ ዕጣን
የዋሻ ሻማ ነሽ እመብርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን (2)
ዳዊት በመዝሙሩ ያነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሃገር የሚሉሽ
እመቤቴ ማርያም አንቺው ነሽ (2)
ቤተልሔም ስሔድ አይሻለው
ቀራንዮም ስሔድ አይሻለው
ፍፁም አትለዪም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ (2)
የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው (4)
እመቤታችን አለች ከጎናቸው

## 9. ደስ ይበለን በጣም

ደስ ይበለን በጣም ደስ ይበለን /2/
በረከቱን ለእኛ ስላደለን

አዝ...
በጨለማ ስንኖር ›› ›› በኃጢአት ተከበን ›› ››
የሕይወትን ብርሃን›› ›› ጽድቁን አበራልን ›› ››
ወደ ምስራቅ እንይ ›› ›› ፀሐይ ወዳለበት›› ››
ጨለማው ልባችን ›› ››ጎህ እንዲቀድበት›› ››

አዝ..
የግሸኗ ንግሥት ደስይበለን የአምላክ እናት ደስይበለን
ሆና ተገኝታለች ›› ›› የሚመኩባት ›› ››
ስምሽን ጠርቼ ›› ›› የምረካብሽ ›› ››
ጎጆ ማረፊያዬ ›› ›› ማርያም አንቺው ነሽ ›› ››
አዝ...
ፀዓዳ እመቤቴ ደስይበለን ሐመልማለ ሲና ደስይበለን
የሕዝቅኤል ደጃፍ ›› ›› የሙሴ ደመና ›› ››
የተዋበች እንቁ ›› ›› የደጎች አዝመራ ›› ››
በማኅፀንሽ ፍሬ ›› ›› ሕይወታችን በራ ›› ››

አዝ...
የፀሐይ እናቱ ደስይበለንማርያም እመቤቴ ደስይበለን
እለምንሻለው ›› ›› እስከ ዕለተ ሞቴ ›› ››
የልቤ ማረፊያ ›› ›› የዘለዓለም ቤቴ ›› ››
አንቺው ነሽ ተስፋዬ ›› ›› ዕፀ መድኃኒቴ›› ››

## 10. በምን በምን

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን /2/
ምሳሌ የላትም (2) ክብሯን የሚመጥን /2/
የሙሴ ፅላት ነሽ የምህረት ቃልኪዳን
የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እኅት የርህሩሃን ርግብ (2)

የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር
ድንግል እመቤቴ ናት የጻድቃኖች በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር (2)
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግሥት
ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ (2)
ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ፅዮን ይድረስሽ ምስጋና (2)

## 11. እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘውትር ነፍሴ (2)
ልቤ ተነሳሳ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍፁም ትኅትና ሊያመሰግንሽ
ፅዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመ ብዙኃን
የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የፅላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና
ክብር ይገባታል ዘውትር ጠዋት ማታ
አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስሯቆት
ያንን የእሳት ባሕር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

## 12. ለማርያም

ለማርያም (2)
እንዘምራለን ለዘለዓለም (2)

አዝ...
የተዘጋች ደጅ ለዘለዓለም ሕዝቅኤል ብሏል ለዘለዓለም
ንጽሕት ናት በእውነት ›› ›› በፍፁም ድንግል ›› አብነት
አድርገን ›› ››እኛምእርሱን ›› ››
በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን (2)

አዝ...
የዋኅት ርግብ ለዘለዓለም ሰላም አብሳሪ ለዘለዓለም
የጨለማ ሕይወቴን ›› ›› ብርሃኔን አብሪ ››
እማፀንሻለው ›› ›› ድንግል ለነፍሴ ›› ››
አደራ ድንግል አንቺ ነሽ ዋሴ (2)

አዝ...
እጅግ የበዛነው ለዘለዓለም ያለኝ ፍቅር ለዘለዓለም
አይነገርም ›› ›› አይወሰንም ›› ››
በእርሷደስይለኛል ›› ›› ሐሴትአደርጋለሁ ›› ››
ስሟንእየጠራውእዘምራለሁ (2)

አዝ...
ንዒ ንዒ ስላት ለዘለዓለም ቀንና ሌሊት ለዘለዓለም
አትለየኝም ›› ›› ለኔስ ቅርቤ ናት ›› ››
ዕፁብ ዕፁብ ብለው ›› ›› አመሰገኗት ›› ››
ክብሯንሊገልፁቢያጥራቸውቃላት (2)

## 13. ትኅትናሽ ግሩም ነው

ትኅትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም (2)
እናቱ ሆነሻል ለመድኃኔዓለም (2)

አዝ...
ንጽሕት ስለሆንሽ እመቤቴ (2) እንከን የሌለብሽ ›› ››
የፍጥረታት ጌታ ›› ›› በአንቺ ያደረብሽ ›› ››
የድንግል መመረጥ ›› ›› ዜናው አስገረመን ›› ››
እሳቱን ታቀፈች ›› ›› የማይቻለውን ›› ››

አዝ...
ምርኩዜ ልበልሽ እመቤቴ (2) ጥላ ከለላዬ እመቤቴ (2)
ጋሻዬ ነሽ አንቺ ›› ›› ለእኔስ መመኪያዬ ›› ››
በዓለም እንዳልጠፋ ›› ›› ሕይወቴ መሮብኝ ›› ››
እንደ ወይን አጣፍጪው ›› ›› ማርያም ድረሺልኝ ›› ››

አዝ...
የምሥራቅ ደጃፍ ነሽ እመቤቴ (2) የሁላችን ተስፋ ›› ››
እሙ ለፀሐይ ጽድቅ ›› ›› የሁሉ ጠበቃ ›› ››
ድንግል የድል አክሊል ›› ›› ድንግል የጽድቅ ሥራ ›› ››
ማርያም መሰላል ነሽ ›› ›› የተዋህዶ ተስፋ ›› ››

## 14. በጎ መዓዛ

በጎ መዓዛ ሽቱዬ ነሽ
በሰው ሁሉ ፊት ዘመርኩልሽ
በአንቺ ጣፈጠ አልጫነቴ
እጠራሻለሁ ነይእመቤቴ

አዝ....
ምሳሌ የሌለሽ ነይ እመቤቴ ዘመዴ ነሽ ነይ እመቤቴ
ያንክፉዘመን ›› ›› ያለፍኩብሽ ›› ››
በፍቅርሽ እሳት ›› ›› ልቤ ነደደ ›› ››
እናትነትሽን ›› ›› ስለ ወደደ ›› ››

አዝ.....
የሰውስ ጉልበት ነይእመቤቴ ምን ይረባኛል ነይ እመቤቴ
ሰረገላዬ ›› ›› መች ያድነኛል ›› ››
ከተሰወረው ›› ›› ክፉ መከራ ›› ››
እድናለሁኝ ›› ››አንቺን ስጠራ ›› ››

አዝ.....
ለስንፍናዬ ›› ›› መቼ ልክ አለው ›› ››
ስለ በደሌ ›› ›› እተክዛለው ›› ››
ለአነጋገሬ ›› ›› ማጣፈጫ ነሽ ›› ››
ተሰምቻለው ›› ›› ድንግል ሆይ ስልሽ ›› ››
አዝ.....
ለመንገዴ ስንቅ ›› ››የረሃቤ መርሻ ›› ››
ለታመመ ሰው ›› ›› ነሽ መፈወሻ›› ››
የተማፀነሽ ›› ›› በስምሽ አምኖ ›› ››
ማን አፍሮ ያውቃል ›› ›› አንቺን ለምኖ ›› ››

## 15. ነዓ ነዓ ሚካኤል

ነዓ ነዓ ሚካኤል ነዓ ነዓ ነዓ ነዓ ሚካኤል ና ወደ እኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

የባሕራንን ጽሕፈት ሚካኤል ነዓ የሞቱን ደብዳቤ›› ››
አንተ ስትለውጠው » » ተደሰተ ልቤ » »
ሚካኤል መሪ ነህ » » ሊቀ መላእክት » »
በኃይልህ ጠብቀን » » አጽናን በእምነት » »

ነዓ ነዓ ገብርኤል ነዓ ነዓ ነዓ ነዓ ገብርኤል ና ወደ እኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልንለእኛ

ከእሳት ውስጥ ተጥለን ገብርኤል ነዓ ኃይሉ ከበዛበት››
ተስፋችን ፅኑ ነው » » ከላይ ከሰማያት » »
መጣልን ገብርኤል » » ከእሳት መሐል ቆሟል » »
የነበልባሉን ኃይል » » በመስቀል ገስጿል » »

ነዓ ነዓ ሩፋኤል ነዓ ነዓ ነዓ ነዓ ሩፋኤል ና ወደ እኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

ፈታሔማህፀንሩፋኤልነዓለጭንቅደራሽሩፋኤልነዓድርሳን
ህየሚያስገርም » » ከደዌፈዋሽ » »
እንዳበራህለት » » የጦቢትንዐይን » »
የእኛንምልቦና » » መጥተህአብራልን » »

ነዓ ነዓ ራጉኤል ነዓ ነዓ ነዓ ነዓ ራጉኤል ና ወደ እኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

ብርሃናዊው መልአክ ራጉኤል ነዓ ሥልጣንህ ግሩም ››
የሃገር ጠባቂ » » መልአከ ሰላም » »
ተስፋዬ ደብዝዞ » » ጨለማ ሲውጠኝ » »
በረድኤትህ ከበህ » » ብርሃንህን ስጠኝ » »

ነዓ ነዓ ዑራኤል ነዓ ነዓ ነዓ ነዓ ዑራኤል ና ወደ እኛ
ምህረት ከአምላክህ ለምንልን ለእኛ

ሰውነቴ ደክሞ ዑራኤል ነዓ በደዌ ሲመታ ዑራኤል ነዓ
ነፍሴን ሲያንገላታት » » የኃጢአት በሽታ » »
ተዓምሩን በማሰብ » » ፀናው ተማፅኜ » »
ዛሬ ዘምራለሁ » » በጠበሉ ድኜ » »

## 16. የስሙ ትርጓሜ

የስሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው
የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው
እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው
ከጉድጓድ ተጥሎ ፍፁም ከሚያስፈራው
ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው
እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን
ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን
የክፉ ሰው ስራው ክፉ ሃሳብ ነውና
በቅንነት መንገድ ከቶ አይሔድምና
የሞቱን ደብዳቤ ለባሕራን ሲሰጠው
ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው
ገና ብላቴና ሳለሁ አንድ ፍሬ
ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምሥጋናን ጀምሬ
ፀጋዬን አብዝቶ ያበቃኝ ለዚህ ክብር
የሚካኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

## 17. እልፍ አዕላፋት

እልፍ አዕላፋት ወትእልፊት ቅዱሳን ትጉኃን መላእክት
ቆመው ለአገልግሎት ፀንተው በአንድነት
ቅዱስ (3) አምላክ በማለት
ኢዮር ራማ ኤረር የመላእክት ሀገር
የሃይማኖት የፍቅር የመላእክት ህብር
እውነት የታየብሽ የመላእክት ክብር

እንፀና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግማሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ
የሳጥናኤል ምኞት እንደ አበባ ረግፎ
ሚካኤል ተሾመ በእምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ ፀጋውን ተገፎ
ቅዱሳን መላእክት በእምነት የፀናችሁ
በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ
ስግደት ዘበፀጋ እንስገድላችሁ

## 18. <u>ጻድቃን ሰማዕታት</u>

ጻድቃን ሰማዕታት በሙሉ
በአካለ ሥጋና በአካለ ነፍስ ያሉ
ከፈጣሪ አማልደው እኛን ያስምራሉ
የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ጻድቃንን ለማየት
ጆሮቹም አይርቁም እነርሱን ለመስማት
የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይል ታደርጋለች
በምልጃቸው እንመን አናመንታ ባንዳች
ጊዜያዊ መሳሪያ ሳያስፈራራቸው
እሳትና ስለት ሳያሳቅቃቸው
ሰማያዊ ተስፋ ስለሚታያቸው
በመከራ ሁሉ ፀኑ በእምነታቸው
ኃጥኡ ነዌ እንኳን በሲኦል እያለ
ስለ ወንድሞቹ ምህረት ከለመነ
እናንተማ ጻድቃን በገነት ያላችሁ
ምንኛ ትረዱን አምነን ስንጠራችሁ
ቀዝቃዛ ውሃ እንኳን በጻድቅ ሰው ስም
የሚያጠጣ ቢኖር ዋጋው አይጠፋም
ብሎ እንዳስተማረን ጌታ በወንጌል
አምነን እንፈፅመው ዋጋ ያሰጣል

## 19. <u>ኦ ፍጡነ ረድኤት</u>

ኦ <u>ፍጡነ ረድኤት</u> (2)
የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ ሰማዕት

ሰላም ላንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት የልዳው ፀሐይ » ››
በጨካኝ ንጉሥ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ » » ስቃይ ያልበገረህ »
» አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሰህ

አዝ...
የፈጣሪውን ስም ፍጡነ ረድኤት ስለመሰከረ » »
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሰይፍ ተመተረ
የስቃይ መሳሪያ » » ያላዘናጋህ » »
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ

አዝ...
የጌታ አገልጋይ ፍጡነ ረድኤት ታማኝ ወታደር » »
ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ስቃይ ቢደርስብህ » » በመታገስህ » »
ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ስምህ

አዝ...
ለሰማው ይደንቃል ፍጡነ ረድኤት ያንተ ሰማዕትነት›
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉም ፍጥረት
ገድልህ ይናገራል » » ክብር እንደተሰጠህ »
» ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖትህ

## 20. <u>ገድሉታምራቱ</u>

ገድሉ ተዓምራቱ እጅግ ብዙ ነው
ጣዖትን አዋርዶ የተሸለመው
የተዋህዶ ኮከብ ተክለ ሐዋርያ
አባ ተክለሃይማኖት ዘኢትዮጲያ
ዳግማዊ ዮሃንስ ጠፈር የታጠቀ
ንፁሕ ባሕታዊ ጠላት ያስጨነቀ
የፀጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ
በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስከተለ
ደካማ መስሏቸውበአንድ እግሩ ቢያዩት
ባለ ስድስት ክንፉ ተክለ አብ የኛ አባት
እርሱስ አንበሳ ነው ትናገር ደብረ አስቦ
ሌጊዮን ሲዋረድ ኀፍረት ተከናንቦ
ከካህናት መካከል ኅሩይ ነው ተክለአብ
መጣው ከገዳምህ ልሳለምህ ብዬ
ኢትዮጲያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ወልድ ዋህድ ብለህ ምድሪቱን ቀደስካት
የባረከው ውሃ የረገጥከው መሬት
ጥላህ ያረፈበት ሆኗል ጸበል እምነት
ኑ እና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ
ይሰብካል ተክለ አብ ዛሬም እንደ ጥንቱ

## 21. <u>ያሬድ ካህኑ</u>

ያሬድ ካህኑ ዘመረ (2)
ዘመረ ያሬድ ዘመረ አምላክን አመሰገነ(2)

አዝ...
አርያም በማለትያሬድ ዘመረ ማኅሌትጀመረ ›› ››
ዜማውን ከመልዕክት እያስተባበረ
ምስጋና አቀረበ ›› ›› በዜማ መሳሪያ ›› ››
ፀናፅል አነሳ ከበሮ መቋሚያ

አዝ...

በግዕዝ በዕዝል ያሬድ ዘመረ በአራራይ ዜማ ›› ››
ከብሉይ ከሐዲስ ምስጢር እያስማማ
በዜማው ምልክት ›› ›› የአምላክን መከራ ›› ››
የመስቀሉን ነገር የማዳኑን ስራ
አዝ...
ደሙ እየፈሰሰ ያሬድ ዘመረ በጦር ተወግቶ ›› ›› ሊቀ
ማኅሌታይ በመንፈስ ተቃኝቶ
በጥዑም ልሳኑ ›› ›› በተሰጠው ፀጋ ›› ››
ለንጉሥ እግዚአብሔር ለአልፋ ኦሜጋ

አዝ
ድጓ ጾመ ድጓ ያሬድ ዘመረ ምዕራፍ መዋስዕት ›› ››
ምስጢር ተገልጦለት ከሰማይ መላእክት
የዜማ መሠረት ›› ›› ፈልፈለ ዝማሬ ›› ››
የኢትዮጵያ ኩራት የተዋህዶ ፍሬ

## 22. <u>የቅዱሳን በዓት</u>

ልቦናን የሚመስጥ መዓዛ ዕጣኗ
ህሊናን ያድሳል ዝማሬ ድጓዋ
የቅዱሳን በዓት የጸሎት ዋሻቸው
ቤተክርስቲያን ናት አንባ መጠጊያችን
የመላእክት ዜማ የአዕዋፍ ዝማሬ
የሚለቀምባት የትሩፋት ፍሬ
ይዘምሩላታል በአንድነት ተባብረው
የሌዋዊው በትር ፀናፅል ከበሮ
ወራዳዋን ዓለም የናቋት በቅድሚያ
የእምነት አርበኞች ያገኟት በፍልሚያ
የገድላቸው ተዓምር መቦግቦጊያ መቅረዝ
የሰማዕታት አክሊል የሥራቸው ደሞዝ
ከኃጢአት ድንኳን መውጣቴ ነው ዛሬ
የቅዱሳን በዓት ልትሆነኝ ሃገሬ
መድርሻዬ ይሁን ከመቃብራቸው
ይፈወሳልና ተረፈ አፅማቸው

## 23. <u>ታማልደናለች</u>

ታማልደናለች (2)
ማርያም(2)ቤዛዊተ ዓለም
ሚካኤል መልአክ ሊቀ መላእክት
ዘአውረድከ (2) መና ከደመና (2)
ገብርኤል መልአክ አብሳሬ ትስብዕት
ዘአብሰራ (2) ለማርያም ንጽሕት
ሩፋኤል መልአክ ሊቀ መላእክት
ዘአብርሃ (2) ዓይኑ ለጦቢት (2)
ዑራኤል መልአክ ለዕዝራ ነቢይ
ዘአስተዮ (2) ፅውዓ ልቡና (2)
ሰሎሞን ይቤላ (2)
ርግብየ ሠናይትየ ሰሎሞን ይቤላ (2)
ገብረ መንፈስ ቅዱስ (2)
ሐዋርያ (2) ዘእስክንድርያ (2)
ተክለሃይማኖት (4)
ሐዋርያ (2) ዘኢትዮጵያ (2)
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ (2)
አዕማደ (2) ቤተክርስቲያን (2)

## 24. <u>ንሴብሖ ለሥላሴ</u>

ንሴብሖ ለሥላሴ (2)
ክበር ተመስገን አምላከ ሙሴ (2)
የእኛ አማላጅ እናታችን (2)
ነይ ነይ ወደ እኛ እመቤታችን
ፈጥነሽ ተገኚ ከመሐላችን
ና ወደ እኛ ሚካኤል (2)
መልአከ ምክሩ ለልዑል
ከእግራችን ይውደቅ ሳጥናኤል
ና ወደ እኛ ገብርኤል (2)
ከእሳቱ አውጣን ከነበልባል
በክንፍህ ጥላ እንጠለል
ና ወደ እኛ ዑራኤል (2)
እንደ ቅዱስ ዕዝራ ሱቱኤል
ጥበብን ስጠን ማስተዋል
ና ወደ እኛ በፈረስ (2)
የልዳው ሰማዕት ጊዮርጊስ
ገድልህን ሰምተን እንፈወስ
ና ወደ እኛ ተክለሃይማኖት (2)
ይጠብቀናል ያንተ ጸሎት
ፀንተን እንድንቆም በሃይማኖት

## 25. <u>አምላከ እስራኤል</u>

አምላከ እስራኤል ታማኝ ጌታችን
ለእስራኤል ለሙሴ የሆንከው መድኅን
ፈርዖን አንተን ረስቶ በትዕቢት ቢገን
ለእስራኤል አርበኛ መረጥከው ሙሴን
አማላጅ ነው <u>ሚካኤል (</u>2) የአምላክ ባለሟል /2/
ለነሙሴ ለህዝበ እስራኤል /2/
ፈርዖን እንደገና ልቡን እያጽናና
ሲከታተላቸው በፈረስ በፋና
ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና
ሌሊት በብርሃን ቀኑን በደመና
ፈርዖን እንደገና ልቡ ተፀፅቶ
ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
እስራኤል ተጨንቀው መሄጃቸው ጠፍቶ

አፅናናቸው ሙሴ የአምላክን ስም ጠርቶ
ሙሴ እንደታዘዘው አነሳ በትሩን
እጁንም ዘረጋ ገሠጻት ባሕርን
እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ
በደረቅ አለፉ እስራኤል በተራ
በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳኢው መልአክ ጠባቂ የእስራኤል
የመላእክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል
በአፎምያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላእክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሊቀ መላእክት
መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሃለን እንድጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ጻድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

### 26. አማልደን ስንልህ

አማልደን ስንልህ ስማን እዘንልን /2/
አፅናን አረጋጋን (2)
ገብርኤል የእኛ መመኪያ አባታችን
እግዚአብሔር እራሱ ክብርን አቀዳጅቶህ
ለተልዕኮ እንድትፈጥን ያረገህ የሾመህ
እንደ ሦስቱ ህፃናት አንተን እንደጠሩት
ዛሬም አውጣን ገብርኤል ሆይ ከነፍሳችን ጠላት
እምነት አለን እያልን ትተናል ምግባርን
እባክህን ሊቀ መልአክ እንድናስብ እርዳን
መላእክትን ሁሉ ያረጋጋሀቸው
አንተ እኮ ነህ ኃያል መልአክ ፅኑ ቁሙ ያልካቸው
እኛስ እናምናለን በአማላጅነትህ
በተሰጠህ የአምላክ ፀጋ ኃይላችን አንተ ነህ
የምስራች መልአክ ተብለሀልና
ደስ አሰኘን ደስታን ስጠን ተጨንቀናልና
ኢትዮጵያንም ታደግ ተዋህዶን ጠብቅ
ሊቀ መልአክ በል ቁምልን ሰይፍህንም ታጠቅ
ሠራዊትህ ከበው እነርሱ ያፅናኑን
ዘወትርም ሳትርቀን ሰላምን ለግሰን

### 27. ሰአሉ ለነ

ሰአሉ ለነ ቅዱሳን መላእክት /2/
ሰአሉ ለነ ጻድቃን ሰማዕታት
ኀበ አምላከ ምህረት ሰአሉ ለነ
ለምኑልን ቅዱሳን መላእክት
ለምኑልን ጻድቃን ሰማዕታት
ወደ አምላከ ምህረት ለምኑልን
አንተ የመረጥከውን ማን ይከሳል
ያፀደከውን ማን ይወቅሳል
ለሚገባው ክብርን መስጠት
ታዟልና በመሕጻፍት
ያከበርካቸው ባሪያዎችህን
እናከብራለን ቅዱሳንህን (2)
ሁሉ መዳንን እንዲይዙ
የሚላኩ የሚያግዙ
ሠርክ በፊትህ እየቆሙ
ጥዑም ቅዳሴን እያሰሙ
በምስጋቸው የሚያከብሩህን
እናከብራለን መላእክትህን (2)
ጤዛ ልሰው ዳዋ ጥሰው
ዋዕይ ቁሩንም ታግሰው
በየፍርክታው በየዱሩ
ሌጦ ለብሰው እየዞሩ
በፅናታቸው የሚያከብሩህን
እናከብራለን ጻድቃንህን (2)
እንደሚታረዱ በጎች ሆነው
አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው
ስለ ስምህ እየተጠሉ
ከአንበሳ ጋር እየታገሉ
በተጋድሎአቸው የሚያከብሩህን
እናከብራለን ሰማዕታትህን (2)
ከህያው ቃልህ እየጠቀሱ
መናፍቃንን ድል እየነሱ
በገዛ ደምህ የዋጀሀትን
ቤተክርስቲያንን የጠበቋትን
በህይወታቸው ያስደሰቱህን
እናከብራለን ሐዋሪርያትህን (2)

### 28. ለዓለም ሰበኩ

ለዓለም ሰበኩ ወንጌልን
ጴጥሮስ ጳውሎስ ቅዱሳን
የፈጣሪን ቃል እያወጁ
ሕይወትን ቀድመው ተወዳጁ
የመዳንን ቃል የነገሩ
ንፁሐን ናቸው የከበሩ
የልዳው ፀሐይ ጊዮርጊስ
ሰማዕተ ኢየሱስ ክርስቶስ
ሹመቱን ትቶ ተድላውን
አገለገለ አምላኩን
ሞቶ ተነስቶ መሰከረ
የጽድቅን ጠላት አሳፈረ

አልሰግድም ብላ ለጣዖት
አንገቷን ሰጠች ለስለት
ዓለምን ንቃ የመነነች
የነፍሷን ጌታ የፈለገች
ደሟን ስለጽድቅ ያፈሰሰች
ቅድስት አርሴማ ክብርት ነች
ገብረ ክርስቶስ አረጋዊ
ገብረ ኢየሱስ ሰማያዊ
በፆም በጸሎት ተጋድለው
ጠላት ሰይጣንን ድል ነስተው
በክብር ወረሱ ገነትን
የጽድቅ አክሊልን ፀጋውን
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጻድቅ
የሚላክለት መብረቅ
ምድራዊ ምግብ ያልቀመሰ
ፀጉሩን እንደ ልብስ የለበሰ
ህዝቡ በኃጢአት በረከሰ
በአናቱ ቆሞ አለቀሰ
ተክለሐይማኖት ሐዋርያ
ሰባኬ ወንጌል ሃሌ ሉያ
ህዝቡን በፀጋ ይባርካል
ጠበሉ ድውይ ይፈውሳል
በቃልኪዳኑ የሚያስምር
በእውነት ታላቅ ነው የእርሱ ክብር
ካህነ ልዑል ላሊበላ
የጽድቁ ዜና ምድርን መላ
በሰማይ ዓይቶ ሥርአትን
ድንቅ አድርጎ ሰራው መቅደሱን
ቢያዝን ቢራራ ለምስኪን
ሰጥቶ ጨረሰ ገንዘቡን

### 29. <u>አንቺን የያዘ ሰው</u>

አንቺን የያዘ ሰው ምን ይጎድልበታል
በምልጃሽ በረከት ቤቱ ሞልቶለታል
ዘር መከር ባይኖረው ጎተራው ባይሞላ
ሁሉም ይሸፈናል በረድኤትሽ ጥላ (2)
በረከትሽ ብዙ የደናግል ገንዘብ
የምስኪናን እናት የርሁባን ቀለብ
ለሁሉ መጋቢ ፀጋሽ የማይጎድል
ስምሽ ጥዑም ምግብ ከረሃብየ ሚያስጥል (2)
አንቺ ብትመጪ ከምስኪኗ ቤቴ
እንደ መጥምቁ እናት በዛልኝ ሃሴቴ
የሐዲስ ኪዳን ቁርባን መንበር ጠረጴዛ
ጽድቅን አሽተትን የሕይወትሽን መዓዛ (2)
ልቤ ተጠራጥሮ ኪዳንሽን ካልከዳ
ልመናም አልወርድም አልይዝም አቁፋዳ
ሁሉን እየሞላሽ መመገብ ታውቂያለሽ
ቢዝቁት የማያልቅ ፀጋና ሐብት አለሽ (2)
የእግዚአብሔር ማረፊያ ኮሬባዊት ዋሻ
የሕይወት ውሃ ምንጭ የህግ መፍሰሻ
ነበልባል ተዋህዶ ሙሴ አንቺን ዓይቷል
ጫማውን አውልቆ ከፊትሽ ተደፍቷል (2)

### 30. <u>ና ና ሚካኤል ና ና</u>

ናናሚካኤል ናና (2)
አዝኛለሁና በአንተ ልፅናና ና ሚካኤል ናና
የረዳህ አፎምያን ሚካኤል ናና ሰይጣንሲፈትናት ›› ››
አንተ ነህ ያዳንከው ›› ›› ባሕራንን ከሞት ›› ››
ለእነርሱ እንደ መጣህ ›› ›› እኔንም ተራዳኝ ›› ››
ሚካኤል ደግፈህ ›› ›› ለመንግሥቱ አብቃኝ ›› ››
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና ና ሚካኤል ናና

ናና ገብርኤል ናና (2)
አዝኛለሁና በአንተ ልፅናና ና ገብርኤል ናና
ዘመኑ ሲፈፀም ›› ›› አምላክ መምጫው ሲደርስ ››
ገብርኤል አንተ ነህ ›› ›› ያልካት ይበልሽ ደስ ››
ድምጽህን አሰማኝ ›› ›› ነፍሴ ጽድቅን ትልበስ ››
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና ና ገብርኤል ናና

ናና ዑራኤል ናና (2)
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና ና ዑራኤል ናና
ቆመህ ጽዋዕ ይዘህ ዑራኤልናና ለዕዝራ ሱቱኤል ›› ››
ጥበብ አጠጥተህ ›› ›› እውቀት ስታድል ›› ››
ተገለጠ ክብርህ ›› ›› መልአኩ ዑራኤል ›› ››
ድኜ በጠበልህ ›› ›› በአውደ ምህረትህ ላይ ›› ››
እኔም ዘመርኩልህ ›› ››
አዝኛለሁና በአንተ ልጽናና ና ዑራኤል ናና

### 31. <u>ማርያም እንወድሻለን</u>

ማርያም እንወድሻለን (2)
ስለወለድሽ የሕይወት ምግብን
ማርያም እንወድሻለን

አዝ...
ድክመቴን አትይ ማርያም በኃጢአት መውደቄን ›› ››
ተስፋይ አንቺ ነሽ ›› ›› እስከለተ ሞቴ ›› ››
ላልከዳሽ ምያለው ›› ›› ከስርሽ ላልጠፋ ›› ››
ገፀ በረከቴ ›› ›› የሕይወቴ ዋስትና ›› ››

አዝ...
የምዕመናን ውበት ማርያም  ዘውድ አክሊላቸው  ››  ››
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ ››  ››   የመንገድ ስንቃቸው ››  ››
ምስክር ነኝ ላንቺ      ››  ››  እንደ ነቢያቱ      ››  ››
ስጦታ መሆንሽን      ››  ››  ለአዳም ልጆች ሁሉ ››  ››

አዝ...
ሞገስና ጸጋ ማርያም በጌታ ፊት ያለሽ ማርያም
ከሰይጣን መሸሻ ››  ››  ዋስ ጠበቃችን ነሽ  ››  ››
እንዴት ነበር ያኔ ››  ››  ጌታን ስትወልጂው ››  ››
የእረኞቹ ደስታ  ››  ››የመላእክት ዝማሬ  ››  ››

### 32. ምሥራቅ ናት

ምሥራቅ ናት (6)
ቸሩ መድኃኔዓለም ያንተ እናት
ዳዊቱማ ይላል   ››   ይቤሎ ይቤሎ      ››
እመቤቴ ማርያም  ››  የወርቅ ሀመልማል  ››
ምሥራቀ ምስራቃት   ››  የፀሐይ መገኛ  ››
ቅድስተ ቅዱሳን  ››  ለምኝልንለኛ  ››
ምንም ታጥቦ ጭቃ ›› ቢሆን ምስራችን ››
ድንግል አትለይን  ›› ጥላ ከለላችን   ››

### 33. ሞት ነው ረሃብ

ሞት ነው ረሃብ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ /2/
ኃይሉ በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ፀጋው በእኛ ላይ አድሮ እንበረታለን
ከአንተ ርቀው ሸሽተው እየሄዱ
ጠፋባቸው የጽድቅ መንገዱ
በሥጋዊ ጥበብ ሲፈልጉ
በመታበይ ስንቶቹ አንተን አጡ
በተዋህዶ የከበርከው ጌታ
መድኃኔዓለም ሆኑልን መከታ
ስንደክም ምኞት ሲፈትነን
ኃይልን ሰጠኸ በእጆችህ ደገፍን
የዓለም ሰይፍ በእኛ ላይ ተስሏል
ሥጋችንን ሊቆርጠው አድብቷል
ኃይልን ስጠን እንድናሸንፈው
ፀጋህ እኛ የእምነት ጋሻችን ነው
ሐዋርያት ፀጋህ በዝቶላቸው
ስለስምህ ፈሰሰ ደማቸው
ዛሬም ለእኛ ጸጋህን አብዛልን
እንዳንደክም ፈተና ሲገጥመን
ጋሻ ሆነህ እንድትመክትልን
ቸር አምላክ ሆይ ወደ አንተ እንጮኻለን
ቢገጥመንም ችግር ወይ መከራ
አትለየን ጌታ ከእኛ ጋራ

### 34. ወዳጄ ሆይ

ወዳጄ ሆይ እነሆ ውብ ነሽ
የታተመች ፈሳሽ እንከን የሌለሽ
የተዘጋች መቅደስ ንጽሕት አዳራሽ
ሕዝቅኤል ያየሽ የምስራቋ በር
ማንም ያልገባባት ከአምላክ በስተቀር
የልዑል ማደሪያ አማናዊት መቅደስ
ስለ ንጽሕናሽ ምስጋናን እናድርስ
ሁለቱንም የሆንሽ እናትና ድንግል
ማኅደረ መለኮት ወላዲተ ቃል
ያለ ዘርዐ ብእሲ በኅቱም ድንግልና
አምላክን የወለድሽ ሐመልማለ ሲና
ምሥራቀ ምሥራቃት ድንግል ሆይ አንቺ ነሽ
ጨረቃን የምትመስይ ፀሐይን የወለድሽ
የማለዳ ብርሃን ለዓይን የምታሳሺ
ፅዮን እናቴ ሆይ ከጎኔ አትሸሺ

### 35. ተክለ ሃይማኖት ተክለ አብ

ተክለሃይማኖት ተክለአብ
ተክለወልድ ተክለመንፈስቅዱስ
አባታችን አማልደን አስታርቀን
ከፈጣሪ ጋር ከአምላካችን
በሦስት ቀን ሥላሴን ያመሰገንህ
ከጭንጫ ድንጋይ ውሃን ያፈለቅህ
አባታችን ተክለሃይማኖት
አማልደን በኃጢአት እንዳንሞት
እንደ መላእክት ክንፍ የተሰጠህ
ሰማዕት ነቢይ አንድም ካህን ነህ
መምህራችን ሐዲስ ሐዋርያ
አስተምረን የጽድቅ ባለሙያ
እንደ ሡራፌል በሰማይ ሲያጥን
በምድር ላይ ረድዕ ሆኖ ማገልገሉን
በተሰጠው ፀጋ ሲያስነሳ ሙታን
ክህነቱ ከአንተ ዘንድ ናት
አባታችን ፍታን ከኃጢአት

### 36. የሕይወትን መዝገብ

የሕይወትን መዝገብ ቃሉን ያስነበቡህን
የተዋህዶ አርበኞች ቅዱሳን ዋኖችህን
የድካም ዋጋቸው የእምነታቸው ፍሬ
ያማረ ነውና ምሰላቸው ዛሬ
ምሥጢሩ ምንድ ነው ድል የማድረጋቸው
ለሰማያዊ ክብር ለአክሊል ያበቃቸው

የሕይወታቸውን መዝገብ ግለጥና አንብበው
መፍትሔ አለውና ገድላቸው የአበው
ድካም ሲበረታ በመንፈስ ስትዝል
ዙሪያህን ዚከብህ የኃጢአት ማዕበል
ፅናት ትዕግስት አጥተህ እንዳትሰናከል
በጾም ጸሎት በርታ አባቶችን ምሰል
ዓለም እያሪኮ ቢፈትንህም ሥጋህ
ዲያቢሎስም ቢያሴር ከመንገድ ሊያርቅህ
ልትወድቅ አትችልም ምን ቢያይል ፈተና
ካሰብክ የፀኑትን የተዋህዶን ፋና

**37. በዘባነ ኪሩብ**

በዘባነ ኪሩብ ለሚቀመጠው
በእሳት ድንጋዮች ቅጥሩን ላጠረው
ዘምሩ ለእግዚአብሔር ለጌታ ዘምሩ
የተከበረ ነው በሰማይ በምድሩ
ኢሳይያስ ሲያው እጅግ አፈረ
የተፈራ ነው የተከበረ
የሰማይ ደጆች ተንቀጠቀጡ
ለቅዱስ ስሙ ክብርን ሲሰጡ
ያልተቀደሰ ለምጽ ያነደደው
እንዴት ይችላል ሊያመሰግነው
በል ፍቀድልኝ ፍቅር ነህና
ልግባ መቅደስህ ላቅርብ ምስጋና
ዙፋንህ ታየኝ ትምክህቴ ሆይ
ስትመሰገን በሰማይ ላይ
ሲያመሰግንህ ያልተደሰተ
ባይተዋር አልሁን አልውጣ ካንተ
ቅኔ የሞላበት ያንን ሰገነት
ልቀላቀለው ተመኘው በእውነት
ልዘምርልህ ባይገባኝም
ዝም የሚል ልሳን አልሰጠኸኝም

**38. ደስ ይበልሽ**

ደስ ይበልሽ (2)
ማርያም ንጽሕት ድንግል ደስ ይበልሽ
ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ
ሰላም እልሻለሁ ማርያም ድንግል
እንደ ብስራታዊው እንደ ገብርኤል
ለአንቺ የተሰጠሽ ሁለት ድንግልና
አንደኛው በሥጋ ሌላው በኅሊና
ከዓለም ሁሉ ሴቶች ንጽሕት በመሆንሽ
ሰማያዊ መና የተገለጠብሽ
የልዑል ማደሪያ ለመሆን የበቃሽ
የጌታችን እናት በጣም ደስ ይበልሽ
ማርያም ስትጎበኛት ወደ ቤቷ ገብታ
ኤልሳቤጥ ዘመረች በመንፈስ ተሞልታ
በማኅፀኗ ያለው ዘለለ በደስታ
እኛንም ትጎብኘን ከጠዋት እስከ ማታ

**39. ጋሻውን ይዞ**

ጋሻውን ይዞ በፈረስ (2)
እንደምን ያምራል ቅዱስ ጊዮርጊስ
እስጢፋኖስ ሲቀደስ (2)
መንፈስ ይወራዳል ከመቅደስ
ገብረ ክርስቶስ ሙሽራው (2)
ጥሎ መነነ ከጫጉላው
ተክለሃይማኖት አባታችን (2)
ቆመ ጸለዩ ለሃገራችን
ህጻኑ ቂርቆስ ሰማዕት (2)
እናቱን ምራት ወደ ገነት

**40. ቤተ ክርስቲያንን**

ቤተ ክርስቲያን አንተውም ከቶ፣
የሰጠንን አምላክ በደሙ መሥርቶ፣
የሰጠንን ጌታ በመስቀሉ ሞቶ፣
የአምላካችንን ቤት አንተውም ከቶ፤
ሁሉንም በሁሉ በሚሞላው ጌታ፣
ሙሽራው የሆነች ቤቱ ተሰኝታ፣
በክብር በሞገስ በፀጋ ተሞልታ፤
ደምቃ ትኖራለች ለዓለም አብርታ (፪•)
ዲያብሎስ ቢጨርስ ቀስቶቹን በሙሉ፣
ወጥመድ ቢዘረጋ በጉዟችን ሁሉ፤
እንሻገራለን የአምላክን ስም ጠርተን፣
አንዳች አይነካንም እርሱን ተጠግተን፤ (፪•)
በስሙ መሰብሰብ በስሙ መጠራት፣
ስለ ስሙ መኖር ለስሙ መሞት፣
ጠላት ዲያብሎስን ምንም ባያስደስት፣
ይህ ነው ክርስትና ይሄ ነው ሕይወት፤ (፪•)
ከትውልድ ለትውልድ የምናስረክበው፣
ለልጅ ልጅ አውርሰን ደስ የምንሰኘው፤
አይደል ብርና ወርቅ አይደል ሌላ ሀብት፣
ሃይማኖታችን ነው የእኛ ርስት ጉልት። (፪•)

**41. ፅኑ ሰማዕት**

ፅኑ ሰማዕት የእምነት አርበኛ፣
አርሴማ ነይ ነይ ወደኛ፤
>>ቴዎድሮስ አትናስያ>> በስእለት ያገኙሽ፣
››ብሉይን ከሐዲስ›› ጠንቅቀሽ የተማርሽ፣
›› በፍጹም ትኅትና ›› በእምነት የፀናሽ፣

››እርሴማ ልዩ ነሽ ›› አምላክ የመረጠሽ፤
›› ›› ውበትም ሐሰት ነው›› ›› ደም ግባትም ከንቱ፣
›› ››ንብረት ትዳር ሁሉ ›› ›› ኃላፊ ውእቱ፤
›› ›› ንግሥት መባልን ›› ›› በፍጹም ሳትሻ፣
›› ››ዓለምን በመናቅ ›› ›› ገባች ወደ ዋሻ፤
››አረመኔው ንጉሥ›› ቢያሠቃይሽም
››ሕይወቴ ክርስቶስ ›› ነው ብለሽ በልብሽ፣
›› እንገትሽን ለሰይፍ ›› አሳልፈሽ ሰጠሽ፣
››ክብርሽም ተገልጾ ›› ለዓለም አበራሽ፤
››አርአያ ልትሆኝን›› ለኛ ለሁላችን፣
››ፈጽመሽ አሳየሽ ›› ታላቅ ተጋድሎሽን፤
››ይህን ዓለም ድል መንሣት›› አቅቶናልና፣

## 42. ትንሳኤሽን ያሳየን

ትንሳኤሽን ያሳየን (፪•)
ውዲቷ ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር
የአባቶች ዘመን ተመልሶ እንድናይ፣
አለን ኢትዮጵያ ውስጥ የፍቅር ራእይ፤
ትሣኤሽን ያሳየን
ትቢያሽን አራግፊ ሐዘንሽን ሽረሽ፣
ዳግም ትነሻለሽ ሀገሬ እንደ ድሮሽ፣
ያልታዘዘች ሀገር ለእግዚአብሔር ሥርዓት፣
አያጣትምና ዘወትር ፍርሐት፤
ትንሣኤሽን ያሳየን
ከቊጣው አምልጣ ሰላም እንድታገኝ፣
ሰውና ሰው ታርቆ ሳሊናው ይገናኝ፤
ይቅርታ ታላቅ ነው ቊስልን ይሽረዋል፣
ጸብ ግን እስከ ዛሬ እነማንን ጠቅሟል፤
ትንሣኤሽን ያሳየን
ቂምና በቀልን ለትውልድ ያቄዩ
በማይበርድ እሳት ፍህም ኋላ ይጋያሉ።

## 43. ተዋሕዶ

ተዋሕዶ ሃይማኖቴ፣
የጥንት ናት የእናትና የአባቴ፤
ማዕተቤን አልበጥስም፣
ትኖራለች ለዘለዓለም፤
የግብጽን ከተሞች በደም ገንብተናል፣
በመግደል ጽድቅ የለም ሞተን ግን ኖረናል፤
ማዕተብሽን ፍቺ በጥሺ ቢሉኝ፣
እኔስ ከነ አንገቴ ውሰዱት አልኩኝ፤
ጴጥሮስ ተሰቀለ ጳውሎስ ተሰየፈ፣
ተዋሕዶ እያለ ኧረ ስንቱ አለፈ፤
ሌሎችም በእሳት በሥቃይ አልፈዋል፣
ዘመን የማይሽረው ታሪክን ጽፈዋል፤
ፊተኛ ነንና እንዳንሆን ኋለኛ፣
ሕዝቤ ተነቃቃ ተነሥ አትተኛ፤
ፀሐይ ከጠለቀች እንዳይሆን ጨኸቱ፣
የተዋሕዶ ልጆች አሁን ነው ሰዓቱ፤
ዐይተን እንዳላየን ስንት አሳልፈናል፣
የእርሱ ፍቃድ ይሁን ብለን ዝም ብለናል፤
አሁን ግን ይበቃል ዝምታው ይሰበር፣
ይገለጽ ይታወቅ የተዋሕዶ ክብር።

## 44. ኦ ክርስቶስ

ኦ ክርስቶስ ኦ አምላክ ብሩህ ነህ
ልቦናዬን አብራው በጥዑም ቃልህ
አዝ...
የታቦር ተራራ ክርስቶስ የሲና ልምላሜ ›› ››
ምነው ሙሴ በሆንኩ ›› ›› እንዳይህ ቀድሜ ›› ››
የዮርዳኖስ ውኃ ›› ›› በላይህ ሲፈላ ›› ››
ዮሐንስን በሆንኩ እንዳይህ በተድላ
አዝ...
ነበልባል ሐመልማል ክርስቶስ ተዋህዶ ሲና ›› ››
ሙሴ ከሩቅ ሆኖ ›› ›› ተመልክቷልና ›› ››
በቀረበ ጊዜ ›› ›› ነገሩን ሊረዳ ›› ››
ለእስራኤል ሾምከው ሁሉን እንዳይጎዳ
አዝ...
ሙሴ በበትሩ ክርስቶስ ኤርትራን ሲመታ ›› ››
ተሻገሩ እስራኤል ›› ›› በፍጹም ደስታ ›› ››
ያልተደሰቱማ ›› ›› የፈርኦን ሠራዊት ›› ››
እየተሰጠሙ ቀሩ ወደ ኋሊት
አዝ...
ትንቢቱ ደረሰ ክርስቶስ የኢሳይያስ ›› ››
ድንግልም ወለደች ›› ›› በመንፈስ ቅዱስ ›› ››
ምነው ባደረገኝ ›› ›› እንደነ ሰሎሜ ›› ››
ጌታዬ ሲወለድ ለማመስገን ቆሜ
አዝ...
ሐዋርያት ሁሉ ክረስቶስ ዞረው ያስተማሩት ›› ››
ወንጌልህ ብርሃን ነው ›› ››የዓለም መድኃኒት ›› ››
ዮሐንስ እንዳለ ›› ›› ጥምቀት ለንስሐ ›› ››
ተጠምቄዋለሁ የጎንህን ውኃ
አዝ...
ሚካኤል በቀኝህ ክርስቶስ ገብርኤል በግራ ›› ››
ቅውማን የሆኑ ›› ›› ሁሉም በየተራ ›› ››
ሱራፌል ኪሩቤል ›› ›› ዓይናቸው የበዛ ›› ››
ያመሰግኑሃል አንተን የዓለም ቤዛ

## 45. <u>ከወገኔ ጋራ</u>

ከወገኔ ጋራ እዘምራለሁ
በደስታ በሐሴት ስሙን እጠራለሁ
ምግብና መጠጤ አምላኬ ነውና
ዘውትር አቀርባለሁ ክብርና ምሥጋና
ሕዝቡ ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያን
ሲዘምር ደስ ይላል በአንድነት ሆነን
በረከት የሞላው ዝማሬው ይገርማል
ከዕጣኑ ጋራ ወደ ላይ ይወጣል (2)
ቀሳውስቱ ሌሊት ማኅሌት ሲያቀርቡ
ከመላእክቱ ጋር ወረብ ሲወርቡ
ብርሃንን ለብሰን በደስታ ስንዘምር
ትዝታው ልዩ ነው ጎሊናን ሲሰውር (2)
ራዕይ ነውና ኑና ተመልከቱ
ሰዎች ሲዘምሩ እንደ መላእክቱ
የጽጌው ማኅሌት የትንሳኤው ደስታ
ልዩ ዝማሬ ነው እንዳይመስለን ተርታ (2)

## 46. <u>ደስ ይበለን</u>

ደስ ይበለን ደስ ይበለን
አምላክ አለ መሐላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ስራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምህረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን ዕድሜ ለጨመረልን
ለንስሐ ጊዜ የሰጠን
ኃጢአትህን ይታገስሃል
በቸርነት አምላክ ያይሃል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥእ የጽድቅ ሕይወት
እልል በሉ የኀበኛችሁ
በቸርነት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑት ዝምም አትበሉ
ድንግል ማርያም ትጸልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር እንኖራለን
በፅኑ ፍቅር አምላክ ባደለን

## 47. <u>ነይ ነይ</u>

ነይ ነይ ማርያም ነይ ነይ
ድንግል ሆይ ነይ ነይ
ያን የእሳት ባሕር ከቶ እንዳላይ
በሐመረ ኖኅ የተመሰልሽው
በአሮን በትር የተመሰልሽ ው
የምስራቋ በር (2) ቶሎ ድረሽ
በተራራማው በኤፍሬም ሃገር
እንግዳ የሆንሽ ለኤልሳቤጥ በክብር
ነይልኝ ወደ እኔ (2) ካንቺ ጋር ልኑር
ዓለም ከብዶብኝ ተጨንቄአለሁ
ኃዘን በዝቶብኝ ብቸኛ ሆኛለሁ
እረ ነይ ድንግል ሆይ (2) እጠራሻለሁ
ጥበብ አንቺ ነሽ ለሲሎንዲስ
ብሎ ሚጠራሽ ሱላማጢስ
አትቅሪ ድንግል ሆይ (2) በጅሽ ልዳሰስ
ምሥጢር የገለጥሽ ለሕርያቆስ
ፈጥነሽ ያማለድሽ ለቤተ ዶኪማስ
ነይልኝ ድንግል ሆይ (2)ልቤ ይፈወስ
ድንግል ቀርባለች ጩኸቴን ሰምታ
የኃጢኣቴ ገመድ እስሬ ተፈታ
አከብራታለሁ (2) ልጇ በእልልታ

## 48. <u>ስምሽን ጠርቼ</u>

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ
የምፅናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምሥጋና
ጨለማው ውጦኝ በጠላት ሃገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
የዓለሙን መድኅን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሃገር ወጥቼ
በአሕዛብ ሃገር ስኖር ሸሽቼ
ደርሰሽ አፅናንተሽ አከበርሽኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰው ታድሞ
አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት ሃሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእመ አምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም
እናት አባቴ ባያስታውሱኝ
ይህች ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አውሎ ነፋሱን ባሕሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ

አላቋርጥም ያንቺን ምሥጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና
ክፍዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ
አንቺን መውደዴን አያስተውኝ
በአሕዛብ መሐል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ጠላቴ ደርሶ ቢያገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምሥጋና
ውለታሽ ድንግል አለብኝና

## 49. ሥላሴን አመስግኑ

ሥላሴን አመስግኑ (2)
የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ
በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ምስጋና ይገባል ከምንም በፊት
ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረ ጌታ
ምስጋና ይገባል ከጠዋት እስከ ማታ
ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰገኑት
መላእክት በሰማይ ለሚዘምሩለት
እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን
በሰማይ በምድር እንጠራሃለን
ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ
ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ
ሥላሴ አንባዬ ክብሬ ናቸውና
ሁሌ ይጠሩኛል በሕይወት ጎዳና

## 50. የቤሩቱ ኮከብ

የቤሩቱ ኮከብ የልዳው አንበሳ
ሦስት ጊዜ ሞቶ ጊዮርጊስ ተነሳ
በተጋድሎ ፀና ቅዱስ ጊዮርጊስ እውነት መሰከረ ››
ኃያሉ ጊዮርጊስ ›› ›› በሠይፍ ተመተረ ›› ››
የልዳው አንበሳ ›› ›› ጠላት ያልገዛህ ›› ››
ሰይጣንን ተዋጋ ›› ›› ጎልማሳው ሥጋህ ›› ››
ዱዲያኖስ ተቆጣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ፅናትህን አይቶ ›› ››
ሊቀጣህ ተነሳ ›› ›› በትዕቢት ተሞልቶ ›› ››
በአንተ ላይ ወገኑ ›› ›› ሰባ ነገሥታት ›› ››
ከምድረ ገፅ አንተን ›› ›› ፍፁም ለማጥፋት ›› ››
ከመበለቷ ቤት ›› ›› ጊዮርጊስ ተዓምር ሰራ ›› ››
ለምፃምን አነፃ ›› ›› ዕውራን አበራ ›› ››
ሰባት አክሊላትን ›› ›› ጊዮርጊስ ተቀበለ ›› ››
ስለጌታው ፍቅር ›› ›› በአደባባይ ዋለ ›› ››
ዝክርህን አዘክሮ ቅዱስ ጊዮርጊስ ስምህን ለጠራ ›› ››
በሥጋም በነፍስም ›› ›› የለበት መከራ ›› ››
ደራጎንን አጥፋው ›› ›› አርቅልን ከእኛ ›› ››
በዝሙት በኃጢኣት ›› ›› ነግሶብናልና ›› ››

## 51. የብርሃን አክሊል ናት

የብርሃን አክሊል ናት ድንግል እናታችን
ከሰማይ እያበራች ደስ አለው ልባችን
ፍቅርሽም ሰላምሽም ድኅነት ይሁነን ኦ ኦ
ፍጥረት <u>በሙሉ</u> (2) ፊትሽ ይወደቃሉ
ፀጋሽ <u>ይድረሰን</u> (2) ይሰጠን እያሉ
የኔ ልብ ምን ጽድቅ አለው አንቺን ለማስተናገድ
የኃጢአት ጎተራ ነው የተሞላው በስስት
ኧረ እንዴት (2) ድንግል ትኑርበት ኦ ኦ
አትጸየፍም የኔን ልብ ታሰናዳዋለች
ስለ ኃጢአቴ የኔ እናት ምልጃን ታቀርባለች (2)
ልባቸውን የዘጉ ድንግልን ለማስገባት
ጎሊናቸው ይመለስ እንጸልይ ለዚህ ጥፋት
አምላክን ይዛ ነው ድንግል የምትመጣው ኦኦ
እርሷን ስንመልስ ጌታን ነው የምናስቀይመው (2)

## 52. ወደ ማደሪያው

ወደ ማደሪያው ገብቼ ልስገድ ለእግዚአብሔር
ምሥጋናንም ላቅርብ ስለስሙ ክብር
አድርጎልኛልና አመሰግነዋለው
በአፀደ መቅደሱ እሰግድለታለሁ
ከፊቱ ለመቆም ማልጄ እነሳለሁ (2)
ለስሙ ልንበርከክ ለእርሱ እንደሚገባ
ስእለቴን ልፈፅም ላቅርብለት መባ
ወደ አደባባዩ በምሥጋና ልግባ (2)
አስር አውታር ባለው በበገና
በመላእክቱ ፊት ለማቅረብ ምሥጋና
የአፌንም ነገር ሰምተኸኛልና (2)
አሸበሸባለው ድምፄን አሰምቼ
በቤተ መቅደሱ ሌሊት ተገኝቼ
እንደ ካህናቱ እጆቼን ዘርግቼ (2)
በመከራዬ ቀን ሆኖኛል መከታ
ቤቱ ተገኝቼ በፍፁም ደስታ
የከንፈሬን ፍሬ ልሰዋ በእልልታ (2)

## 53. ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ማርያም እጮሃለሁ
ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወድሰኒ ልጄ በይኝ
›› ›› በሰርክ ጸሎት ላይ ›› ›› ዜማ ስናደርስ
›› ›› ድንግል ትመጣለች ›› ›› በቤተ መቅደስ
›› ›› የብርሃን ምንጣፍ ›› ›› ከፊቷ ተነጥፏል
›› ›› ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ ›› ›› ያመሰግናታል

›› ›› አባ ሕርያቆስም ›› ›› ምስጋና ያደርሳል
›› ›› የቅዳሴው ዜማ ›› ›› ልብን ይመስጣል
›› ›› በጎ ነገር ልቤ ›› ›› አወጣ እያለ
›› ›› ዳዊት በገናውን ›› ›› እየደረደረ
›› ›› የንጽሕናችን ›› ›› መሠረት ነሽና
›› ›› አንቺን ለማመስገን ›› ›› ልቦናችን ይብራ
›› ›› ተፈሥሒ ድንግል ›› ›› ኦ ቤተልሔም
›› ›› ከአንቺ ተወለደ ›› ›› መድኃኔ ዓለም
›› ›› ቅዱሳኑ ሁሉ ›› ›› ዙሪያሽን ከበዋል
›› ›› አባ ጊዮርጊስም ›› ›› ንዒ ድንግል ይላል
›› ›› በወርቅ ዙፋን ላይ ›› ›› ተቀምጠሽ ሳይሽ
›› ›› ልቤ ተሰወረ ›› ›› ድንግል በግርማሽ

**54. ቅዱስ ሚካኤል**

ቅዱስ ሚካኤል (3)
ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ስጋዬ
ፈጥነህ ተረዳኝ ዋስ ጠበቃዬ

አዝ...
አንተ ስለሆንክ ሚካኤል የአምላክ ባለሟል ›› ››
ልመና ፈጥኖ ›› ›› ከአምላክ ያቀርባል ›› ››
የዋህ መልአክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው (2)

አዝ...
ደዌ የፀናበት ሚካኤል ባንተ ይድናል ›› ››
በአደባባይህ ›› ›› ምስክር ሆኗል ›› ››
ከቤትህ መጥቶ የተማፀነ
በቃል ኪዳንህ ህይወቱ ዳነ (2)

አዝ...
ከአምላክ ተሰጥቶ ሚካኤል ክብርህ ያበራል ›› ››
ለጎስቋላው ሰው ›› ›› መጠጊያ ሆኗል ›› ››
ትንሽ ትልቁ ደሀው ሀብታሙ
ለምኖ አግኝቷል ከአምላክ በስሙ (2)

አዝ...
በብሉይ ኪዳን ሚካኤል ከአምላክ ተልከህ ›› ››
ህዝበ እስራኤልን ›› ›› ነፃ ያወጣህ ›› ››
በሐዲስ ኪዳንም ድንቅ ስራ አለህ
በተዓምራትህ ትፈውሳለህ (2)

አዝ...
ባለ መድኃኒት ሚካኤል ያቀተውን ›› ››
ፈዋሽ ጠበልህ ›› ›› ሆኖኛል ኃይል ›› ››
እንደ መፃጉዕ ድኅነት አገኘው
ፈውሰኸኛል ባንተ ተመካው (2)

**55. ለምኚ**

ለምኚ ድንግል ለምኚ (2)
ለኃጥአን (3) አይደለም ለጻድቃን
ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ ለምኚ አዛኝ ርህሩህ ነሽ
›› የጌታዬ እናት ›› ፀጋን የተመላሽ
›› የአምላክ ማደሪያ ›› ለምነሽ አስምሪኝ
›› አማናዊት ፅዮን ›› ከእኔ አትለይኝ
ለምኚ ኃዘንሽ ኃዘኔ ለምኚ ለእኔ ይሁን ድንግል
›› የተንከራተትሽው ›› በሃገረ እስራኤል
›› ትዕግስትሽን ሳየው ›› ልቤ ይደነቃል
›› የኃዘን ዕንባ ጎርፍ ›› ዓይኔን ይሞላዋል
ለምኚ በቀራንዮ አንባ ለምኚ በዚያ በፍቅር ቦታ
›› ከእግረ መስቀሉ ስር ›› ከክርስቶስ ጌታ
›› ለእኛ ተሰጥተሻል ›› እናት እንድትሆኚን
›› ልጆችሽ ነንና ›› ምልጃሽ አይለየን
ለምኚ አንደበቴን ጌታ ለምኚ በምሥጋና ሙላው
›› ደስ ይበልሽ ብዬ ›› እኔም ላመስግናት
›› አንደበቴን ጌታ ›› በምሥጋና ሙላው
›› ደስ ይበልሽ ብዬ ›› እኔም ላመስግናት

**56. ይበራል በክንፉ**

ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው
የአምላክ ስም አለበት ስሙ ሚካኤል ነው
ያሳደገኝ መልአክ ዛሬም ከእኔ ጋር ነው (2)
ከፊቴ ቀደመ ደመናን ዘርግቶ
እንዳልደናፈቅ ጉድባዎቼን ሞልቶ
ዛሬ ላለሁበት ብርቱ ጉልበት ሆነኝ
ሰው ለመባል በቃው ሚካኤል ደገፈኝ
በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ
አለው እስከ ዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ
የሕይወቴን ሰልፎች አለፍኩ ከእርሱ ጋራ
ተጽፏል በልቤ የሚካኤል ሥራ
ፊት ለፊት ተተክሎ ከታናሿ መንደር
ይሰማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር
ይወስደኛል ደጁ እየቀሰቀሰ
ታላቁን በረከት በልቤ አፈሰሰ
ሴኬምን እንዳላይ ክንፎቹን ጋረደ
መራኝ ወደ ሕይወት መዳኔን ወደደ
የአምላኬን ምስጋና ዘወትር እያስጠናኝ
እርሱ ነው ሚካኤል በመዝሙር የሞላኝ

**57. ኃያል ነህ**

ኃያል ነህ አንተ ኃያል
ደጉ መልአክ ገብርኤል (2)

ይውደቅ ይሸነፍ ጠላት
አንተው ተራዳን በእውነት (2)

አዝ...
በዱራ ሜዳ ላይ ገብርኤል ጣዖት ተዘጋጅቶ ገብርኤል
ሊያመልኩት ወደዱ ›› አዲስ አዋጅ ወጥቶ ››
ሲድራቅ እና ሚሳቅ አብድናጎም ፀኑ
ጣዖቱን ረግጠው በእግዚአብሔር አመኑ

አዝ..
ተቆጣ ንጉሡ ገብርኤል በሦስቱ ሕጻናት ገብርኤል
ጨምሯቸው አለ ›› ወደ እቶን እሳት ››
ከሰማይ ተልኮ ደረሰ መልአኩ
ከሞት አዳናቸው በእሳት ሳይነኩ

አዝ..
ከእቶኑ ሥር ሆነው ገብርኤል ዝማሬን ተሞሉ ገብርኤል
ገፍተው የጣሏቸው ›› በእሳት ሲበሉ ››
አልተቃጠለችም የራሳቸው ጸጉር
አዩ መኳንንቱ የእግዚአብሔርን ክብር

አዝ..
ናቡከደነፆር ገብርኤል እጁን ባፉ ጫነ ገብርኤል
ሠለስቱ ደቂቅን ›› ከእሳት ስላዳነ ››
ይክበር ጌታ አለ የላከው መልአኩን
ሊያመልከው ወደደ ስላየ ማዳኑን

**58. <u>የፍቅር እናት</u>**

የፍቅር እናት የሰላም (2)
ይናፍቀኛል ስምሽን ሳልጠራው ስቀር ማርያም
    በሕይወቴ ውስጥ በኑሮዬ
    ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ
    ተደላደለ ልቤ
    አንቺ አለሽና ከአጠገቤ
ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ
ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታዬ እናት ነሽ
ኃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ
    ትላንትም ዛሬ አመስጋኝ ነኝ
    የለም ለነገ የሚያስፈራኝ
    ሜዳው ይሆናል ተራራ
    ልጅሽ ስላላ ከእኛ ጋራ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገዴ
አደራ እናቴ አስቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ ጠላት
ለሚያሳድደኝ አትስጭኝ